**ሳምንታዊ ዜና (ሰኔ 7  ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**በግፍ የተገደሉ ሰማዕታት ሰኔ 1 ቀን ለ3ኛ ጊዜ ታስበው ዋሉ፣ መቼም ቢሆን መቼ የልጆቻችንን ገዳዮች እንፋረዳለን ሲሉ የሟች ቤተሰቦች ለሕዝቡ ጥሪ አቀረቡ፣ በደብረዘይት ጥብቅ ፍተሻ ሲደረግ አመሸ፣ ረሀቡ እጅግ አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱን አለም አቀፍ ድርጅቶች አሳወቁ፣ የእርዳታ እህል እንዳይሰጥ ሲከለከል የነበረው የነመለስ ቡድን የድረሱልኝ ጥሪ ማቅረቡ አስገራሚ መሆኑን ዲፒሎማቶች ገለጡ፣ የረሀብተኛው ቁጥር ከ10 ሚሊዮን በላይ አሻቀበ፣ የኑሮ ውድነቱ እጅግ የከፋ ደረጃ ላይ ደረሰ፣ 20 ሊትር ውሃ 10 ብር መሸጥ ተጀመረ»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዝርዝር ዜና ያንብቡ .......**

ምርጫ 1997ትን ተከትሎ ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም እና ጥቅምት 23 ቀን 1998 ዓ.ም በአምባገነኑ የወያኔ ቡድን በግፍ የተገደሉ ሰማዕታት ቀን ሰኔ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ቸርቸር በሚገኘው በኢንጅነር ኃይሉ ቢሮ ታስቦ ዋለ::

በግፍ የተገደሉት ቤተሰቦች በኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ፈቃድ ሰጪነት በቢሮው ቅጥር ግቢ ተሰባስበው ያከበሩ ሲሆን የሙዋች ቤተሰቦችና ሌሎችም ተገኝተዋል::በዕለቱ የሟቾች ምስል ያለበት ካኔቴራ በመልበስና የሻማ ማብራት ስነ ስርዓት መካሄዱም ታውቋል::

ወያኔ በ1997 ዓ.ም ወርሀ ግንቦት በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ መሸነፉን ተከትሎ በወሰደው ዘግናኝ እርምጃ ንፁሃን ዜጐችን ከ200 በላይ የገደለ ሲሆን ብዙ መቶዎችን አቁስሎ ለአካለ ጐደሎነት ከመዳረጉም ባሻገር አስር ሺህዎችን በየካምፑ አስሮ እንደነበረ የሚታወስ ነው::

እሁድ ሰኔ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ለ3ኛ ጊዜ በፀሎትና በሻማ ማብራት የሟች ቤተሰቦች ተሰበሰበው ያከበሩ ሲሆን በዕለቱም ምሬት የተቀላቀለበት መልዕክት ሲያስተላልፉ እንደነበረም ተደምጡዋል::

በተለይ የሟች እናቶች ዛሬም የልጆቻቸውን መሞት እያስታወሱ እንደተኩስ ለቅሶ እንባቸውን እያፈሰሱ «መቼም ቢሆን መቼ የልጆቻችንን ገዳዮች እንፋረዳቸዋለን» በማለት ሀዘንና እንባ በተቀላቀለበት ስሜት ገልፀዋል::

አረመኔው ወያኔ ገና ለገና ስልጣኔን ልነጠቅ ነው በሚል ፍርሀት ምንም የማያውቀውን ጨቅላ ልጄን ገድሎብኛል ያሉት አንድ እናት በሀዘን የተነሳ እጅግ ሰውነታቸው ተጐሳቁሎ ጠቁረውና ከስተው የታዩ ሲሆን የሁለት

ሙዋች እናቶች በልጆቻቸው መሞት ምክንያት በሀዘን ብዛት እነሱም እንደሞቱ ገልጸው ጊዜው ቢቆይም ገዳዮችን እንፋረዳለን ብለዋል፡፡

ወያኔ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በሕዝብ ድምፅ ወደ መቃብር የወረደበት ዕለት ቢሆንም ባለው ወታደራዊ ኃይል ተጠቅሞ እንደገና የመቃብር አፈሩን ከላዩ ላይ አራግፎ የእውር ድንብሩን ብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ንፁህ ዜጐችን መግደሉ የአለም ሕብረተሰብን ጭምር ያስቆጣ እና ያበሳጨ ሲሆን የወያኔ ቡድን ግን በሰራው ስራ እጅግ ተደስቶ የፍየል ወጠጤን ሲያስዘፍን እንደነበረ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

አጣሪ ኮሚሽን ይቋቋም ብለው የውጭ መንግስታት ባደረጉት ግፊት ወያኔ አጋልጠው አይሰጡኝም ያላቸውን በወቅቱ የደቡብ ክልል ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንት አቶ ፍሬህይወትን የአጣሪ ኮምሽኑ ዋና ሰብሳቢ፤ ምክትል ሰብሳቢ ደግሞ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻን አደርጎ የነበረ ቢሆንም ሰዎቹ ሪፖርቱን በሰሩበት ወቅት ያገኙት መረጃ እጅግ አስደንጋጭ በመሆኑ ያለውን ሀቅ ክደው ለወያኔ ማጎብደድ ህሊናቸው ባለመፍቀዱ ያዘጋጁትን ሙሉ ሪፖርት ይዘው ከሀገር የወጡና ያጋለጡ እውነተኛ የሕዝብ ልጅነታቸውን ያረጋገጡ ሲሆን፣ የተቀሩት የኮሚቴው አባላት ለሆዳቸው ያደሩ ሕሊና የሌላቸው በመሆናቸው ብቻ በንፁሃን ዜጐች ላይ የተወሰደው እርምጃ ትክክል ነው በማለት ሸምጥጥ አድርገው ክደው በተወካዮች ም/ቤት ተብየው ማቅረባቸው ሰዎቹ በኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ጥቁር መዝገብ ውስጥ መስፈራቸው አይዘነጋም፡፡

ወያኔ በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ፣ በጋምቤላ ፤ በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ (ሎቄ) ከ1985 ዓ. ም. እስከ ዛሬ ድረስ ንፁህ አትዮጵያውያኖችን በአየአደባባዩ ገድሎ በአንድ ጉድጓድ እየቀበረ የመጣ ቡድን ሲሆን፣ አሁንም በዚህ ድርጊት የገፋበት መሆኑም ታውቋል፡፡

በተለይም በቅርቡ በአዲስ በአበባ ውስጥ በስብሃት ነጋ መሪነት የሚንቀሳቀሱት ማፊያ በድን ንፁሃን ዜጐችን እያፈኑና እየገደሉ መሆኑ ለዚሁ ተግባር ማረጋገጫ እንደሆነም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አፅንኦት ሰጥተው ይገልፃሉ፡፡

ወያኔ ካለበት ፍርሃትና ስጋት የተነሳ የራሱን ጥላ እያየ እየደነበረ የሚገኝ ቡድን ሲሆን ባለፈውም ሳምንት ቅዳሜ በደብረዘይት ከተማ « የታጠቀ ኃይል ገብቷል፣ የጦር መሣሪያ ተጭኖ ገብቷል» በሚል የከተማዋን ነዋሪዎችና

ተንገሮች በፍተሻ የቁም ስቅል ሲያሳያቸው እንዳመሸ ከደብረዘይት ከተማ የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

ባደረበት ውስጣዊ ስጋት የተነሳ የሚያደርገው ሲጠፋው በየሄደበት ያይንህ ቀለም አላማረኝም እያለ በርካታ ምሁራንን ከየአደባባዩ እያፈሰ ወደ እስር ቤት እያጐረ የሚገኘው ወያኔ በአዲስ አበባ ሲያደርግ የነበረውን ፍተሻ ወደ ደብዘረይት ያስፋፋው ካለበት ስጋት የተነሳ መሆኑን ውስጥ አዋቂዎች ይገልፃሉ፡፡

በተለይም ቅዳሜ በደብረ ዘይት ሲደረግ የነበረው ፍተሻ እጅግ ጥብቅ ከመሆኑም ባሻገር ከናዝሬት ደብረ ዘይት ፤ከደብረ ዘይት አዲስ አበባ መግቢያና መውጫ መስመሮች ላይ ቁጥሩ እጅግ በጣም ብዙ የሆነ መኪኖች ለፍተሻ ቆመው ለሰዓታት ያህል የትራፊክ እንቅስቃሴ ቆሞ እንደበረም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

ከቀኑ 10 ሰዓት የጀምረው ይኸው ድንገተኛ ፍተሻ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ድረስ በደብረዘይት መግቢያና መውጪያ ላይ ሁለቱም በሮች ብቻ ሳይሆን በከተማዋ ውስጥ ለውስጥም ተመሳሳይ ፍተሻ ማድረጋቸው ሕዝቡ በጊዜ ወደቤቱ እንዳይገባ ሲያንገላቱት እንዳመሹም የደረሰን ዘገባ አስረድቱዋል፡፡

በሌላ በኩል በሀገሪቷ የተከሰተው ረሀብ ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፋ የረሀብተኛው ቁጥር ከ10 ሚሊዮን በላይ ማሻቀቡ ታወቀ፡፡

በሀገሪቷ ረሀብ አልተከሰተም እያለ የውሸት ጡሩንባውን ሲነፋ የነበረው ወያኔም በተከሰተው ረሀብ የድረሱልኝ ጥሪ ማቅረቡም ታውቋል፡፡

ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንዲሉ ከ3 ወር በፊት ሀገር በቀልና አለም አቀፍ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በሀገሪቷ ረሀብ መከሰቱን አረጋግጠው አፋጣኝ እርምጃ ይወሰድ በሚል ቢወተውቱም ጆሮ ዳባ... ያለው ወያኔ በአለም ምግብ ድርጅትና ለጋሽ ድርጅቶች ጩኸት ሳይወድ በግድ አምኖ ጥሪ ማቅረቡ ታውቋል፡፡

የኢኮኖሚ እድገታችን 10 በመቶ ሆኖዋል እያለ ባዶ ጩኸት ሲጮህ የነበረው ወያኔ በሀገሪቱ የረሀብ አደጋ እንደተከሰተ ከወራት በፊት ቢገለፅለትም ደረቱን አሳብጦ ሰፈር ውስጥ እንደሚያውደለድል ጉረምሳ ችግር የለም እያለ ትኩረት ሳይሰጥ በመቅረቱ በተከሰተው ረሀብ የተነሳ በርካታ ዜጐች ለሞት የተዳረጉ ሲሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትም ዛሬ እንደ ደራሽ ውሃ ሙላት በደቡብና

በኦሮሚያ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ ለረሀቡ ተጋልጠው እንደሚገኙ ታውቁዋል፡፡

የወያኔ በድን መሪዎች በቤተ መንግስት ዙሪያ ተኮልኩለው ቀፈታቸውን አሳብጠው ንፁሃን የሀገሪቱ ዜጎች በረሀብና በችግር እንደቅጠል ሲረግፉ የለጋሽ ድርጅቶችም ረሀብ መከሰቱን ገልፀው በአፋጣኝ ለመድረስ ቢሞክሩም አእምሮ የለሽ ግለሰቦች የተሰባሰቡበት ይኸው ቡድን ከመከልከሉም በተጨማሪ እንደ ወንጀለኛ እያደነና ስማቸውን እያጠፋ ሰያጥላላቸው እንዳልነበረ ዛሬ እርዳታ በአስቸኩዋይ ካልደረሰን እጅግ አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ገብተናል፡፡ በዚህም በተከሰተው ሁኔታ ተጠያቂዎች አንሆንም በማለት እየወተወተ መገኘቱ ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑ ዲፕለማቶችን ያስገረመ ሆኗል፡፡

ችግሩ ሳይባባስ በረሀብ ለተጠቁት ወገኖች እንድረስ ሲባል ረሀብ በሀገሪቷ አልተከሰተም እያለ ሲያሾፍ የነበረው ወያኔ ዛሬ ሀቁ አፍጥጦና አግጥጦ ከ10 ሚለዮን ሕዝብ በላይ በረሀብ መጠቃቱን የአለም ምግብ ፕሮግራም ይፋ ሲያደርግና ሌሎችም አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች እውነታውን በማውጣታቸው ተደናግጦ ቀድሞ ማድረግ የሚችለውን አሁን የድረሱልኝ ጥሪ ማቅረቡ በአለም አቀፍ ደረጃ ትዝብት ለይ የጣለው መሆኑ ታውቋል፡፡

ለሚፈጠረው ሁሉ ተጠያቂ አይደለንም በአስቸኩዋይ እርዳታ ይድረስልን እያለ በስምኦን መቻሌ አማካኝነት እየወተወተ ያለው ወያኔ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ የእርዳታ ጥሪ ያቀርቡ የነበሩትን የአለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ጥቅመኞች እያለ እያጥላላና እየሰደበ ለተቸገረው ሕዝብ እንዳይደርሱ እየከለከለ በቤተ-መንግስት ዙሪያ ተኮልኩለው በውስኪና በጮማ ሲወጠሩ ማየት የሚያንገበግብ ነው ያሉት አንድ የአፍሪካ ሀገር ዲፕሎማት ይህ ችግር እንዳይከሰት ብዙ ጥረት ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የነመለስ በድን ፍፁም ሊዋጥለት አልቻለም፡፡

በተለይም በአሁን ሰዓት በደቡብና በኦሮሚያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በረሀቡ ምክንያት በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙ ሲሆን አሁንም ገና የእርዳተ እህል እንዳልደረሳቸውም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከሕዝብ ይልቅ ገንዘብን ፧ ከሀገር ይልቅ ባዕድን እንደ ጣኦት እያመለኩ ያሉት እነ መለስ ዜናዊ ዛሬ የሀገሪቱ ሕዝብ በረሀብ እና በኑሮ ውድነት እየተጠበሰ ባለበት ወቅት እነሱ እንደልባቸው እየተንደላቀቁ በሕዝብ ላይ ማሾፋቸው እንደ ደርግ ባለሥልጣናት የእጃቸውን ማግኘታቸው አይቀሬ ነው

ያሉት  አንድ የአዲስ  አበባ ዩኒቨርስቲ  መምህር  አለምን ጉድ  ያሰኘ  ድራማ እየሰሩ  መሆኑ  ግርም  የሚል  ነው  ብለዋል::

ይህንንም  ሲያብራሩ  እርዳታ  እንለግስ  ያሉ  ድርጅቶችን  እንደ  ጠላት ቆጥረው  መግለጫ  አውጥተውባቸው  እንዳልነበረ  ዛሬ  ደግሞ  እባካችሁ  እያሉ የማስመሰያ  ልመና  ማቅረባቸው  ደግሞ  አሳፋሪና  አሳዛኝ  ነው  ብለዋል::

ዛሬ  በሀገሪቱ  ያለው  የኑሮ  ውድነት  እጅግ  ከፍተኛ  ደረጃ  ላይ  ከመድረሱም በላይ በየቀኑ  ሁኔታዎች  እየተቀያየሩ  ችግሩ  እየተስፋፋና  እያደገ  መጥቷል ያሉት ሌላው መምህር  በኢትዮጵያውያን  አቅም የማይኖርበት  ደረጃ  ላይ  ተደርሷል ሲሉም  ስጋታቸውን ገልፀዋል::

የወያኔ ሹማምንት  ገንዘብ  ከካዝና፣ ጤፍ  ከገጠር፣ ሙክት  ከማደለቢያ፤ ጮማ ከቄራ፣ወስኪ ከቦሌ እንዳሻቸው እያዘዙና እያስመጡ ሲምነሸነሹ ስለሚኖሩ  የኢትዮጵያን ሕዝብ  ችግር  ምን  እንደሆነ ያለማወቃቸውና ሊያውቁ ያልፈለጉ  ቀፈታሞች  ናቸው ያሉት  እኚሁ  መምህር  ገመናቸው  ሲጋለጥባቸው  ደግሞ  ማላዘናቸው  ማንነታቸውን ቁልጭ  አድርጐ  ያሳየ ነው  ብለዋል::

በሱማልያ  ድንበር  አስከብራለሁ  እያለ  በቀን በብዙ  መቶ  ሺህ  ብር  እያወጣ ያለው  ወያኔ  የማያገባው  ገብቶ  እየፈተፈተ  ከመሆኑም  በላይ  የሀገሪቷ  ዜጐች የሚላስ  የሚቀመስ  አጥተው  እየተንከላወሱ  ባለበት  ወቅት  በሱማልያ  ውስጥ ይህንን  ያህል ገንዘብ  ማውጣቱ  እጅግ  አስገራሚ  ነው  ያሉት  አንድ  የመከላከያ መኮንን ሰሞኑንም ይኸው ትዕይንት  በተለያዩ  ወታደራዊ  ክፍሎች  ውስጥ እየተስተዋለ  ነው  ብለዋል::

ግንቦት 26 ቀን  2000 ዓ.ም የመከላከያ አንዱስትሪ  ሲምፖዚየም  ተጠናቀቀ ተብሎ እጅግ  ከፍተኛ  ብር  ወጪ  ተደርጐ  ድግስ ተደግሶ  የከፍተኛ  የጦር  መኮንኖችን ማንበሽበሹ  ስርዓቱ ምን እየሆነ እንዳለ የሚገልጽ ሲሆን ቡድኑ  በገንዘብና  በንዋይ ታውሮ  መገኘቱን  ያሳያል  ሲሉ  እኚሁ መኮንን  ገልፀዋል::

በሰሜን  ዕዝ  በሜ/ጄ/ል  ሳዕረ  መኮንን  የሚመራውን  ጦር ለማታለል  ጥቂት እህል  ቢጤ  አቅምሰው ለጄኔራሎችና  ለከፍተኛ  መኮንኖች  ግን በሽሬ  እና በመቀሌ ድል  ያለ ድግስ  ደግሰው  በውስኪ ሲራጩ  የሰነበቱ  ሲሆን  በአንፃሩም  በአርሲና በሌሎችም  የተቀሩት  የሀገሪቷ  ክፍሎች  በረሀብ  ምክንያት  በርካታ ቁጥር ያላቸው  ዜጐች በየሰዓቱ  እንደቅጠል  እየረገፉ  መገኘታቸው  አሳዛኝ  ነው ሲሉም ጉዳዩን የተከታተሉት እኚሁ መኮንን ገልፀዋል::

በርካታ ዜጐች ከረገፉና የወያኔ ቡድንም ተስፋ ከቆረጠ በኋላ የድረሱልኝ ጥሪ ማቅረቡ እጅግ አለምን ያስገረመ ሲሆን፣ እርዳታው ካልደረሰ ተጠያቂ አይደለንም እያለ መወትወቱ የአለም ምግብ ፕሮግራም ኃላፊዎችን ጨምሮ ሌሎችንም የለጋሽ ድርጅት ተጠሪዎች ያስገረመና ያስፈገገ መሆኑን ለዲፕሎማቲክ ቅርበት ካላቸው ምንጮች ያገኘነው ዘገባ ያስረዳል።

የአለም ምግብ ፕሮግራም በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ እጅግ አስከፊ መሆኑን በመረዳቱ ወደ ሌላ ሀገር ጭኖ የነበረውን እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ እንዲዞር አድርጌያለሁ በማለት መግለጫ ሰጥቷል።ይሁን እንጂ በሀገር ውስጥ መጠባበቂያ ተብሎ የተቀመጠው እህል ወጪ ተደርጐ ለዜጐች እንዳይሰጥ ወያኔ አሁንም በሩን ቆልፎ እንደሚገኝ የገለፁት ለዲፕሎማቲክ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ወያኔ የድረሱልኝ ጥሪ ያቀረበው በተፅእኖ ነው እንጂ ዜጐች ቢሞቱና ቢያልቁ ቅንጣት ታክል ሐዘኔታ የለውም ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

የኑሮ ወድነቱ እጅግ የከፋ ደረጃ ላይ ደርሶ በገጠሪቷ ኢትዮጵያ 1 ጀሪካን ባለሀያ ሊትር ውሃ ከ10 ብር እስከ 15 ብር ፣አንድ ኩንታል በቆሎ 600 ብር እየተሸጠ ወያኔ አይመለከተኝም በሚል የራሱን ሆድ አደር ካድሬዎቹና ባለስልጣናቱ እንዳይቸገሩና እንደ ልባቸው እንዲሆኑ እያሙዋላላቸው እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ፣